# MEMORIAL HERMANN SURGICAL HOSPITAL KINGWOOD
## ፖሊሲ

**የፖሊሲ ርእስ፦** የገንዘባዊ እገዛ ፖሊሲ

**የታተመበት ቀን፦** 02/11/2019
**እትም፦** 3

---

**የፖሊሲ አላማ፦**

የዚህ ገንዘባዊ እግዛ ፖሊሲ (“FAP”) አላማ Memorial Hermann Surgical Hospital Kingwood (“MHSHK”) በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያገለግላቸው ሰዎች በስርአታዊ ዘዴ መለየት እና ገንዘባዊ እገዛ ማድረግ ነው።

MHSHK የMemorial Hermann Health System (MHHS) አጋር ሲሆን በ MHHS ባልተሸፈኑ ዓላማዎችን ላይ ይሰራል። MHHS የሀሪስ፣ ሞንትጎምሪ፣ ፎርት ቤንድ እና ሌሎች በአካባቢው የሚገኙ § 501(c)(3) ካውንቲዎችን የሚያገለግሉ የውስጣዊ ገቢ ኮድ ክፍል ሆስፒታሎችን ያስተዳድራል። MHSHK ግለሰቦችን የመክፈል አቅማቸው ምንም ይሁን ምን ከግምት ሳናስገባ እንዲሁም ያለ ምንም አድልዎ፣ መድህን የሌላቸው እንዲሁም ከበቂ በታች የመድህን ሽፋን ያላቸው ሆነው አስቸኳይ ሕክምና ወይንም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች ለሚሹ ሰዎች በገንዘብ መልክ የሚሰጡ የማህበረሰብ ጥቅማጥቅሞች ለማበርከት በቁርጠኝነት ይሰራል።

**ተግባራዊ የሚሆንባቸው ቦታዎች፦**

ይህ FAP በስቴት-ፈቃድ የተሰጠው የሆስፒታል ተቋም የ MHHS ዓላማን ወደፊት ለማስኬድ የተቋቋመው Memorial Hermann Surgical Hospital Kingwood ላይ ይተገበራል።

**የፖሊሲ መግለጫ፦**

1. ርህራሄ እና ወካይነት የ MHSHK እሴቶች እንደመሆናቸው መጠን፣ MHSHK ለተቸገሩ ታካሚዎች የገንዘብ እገዛ የማድረግ ፖሊሲ ይከተላል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ታካሚዎች በ MHSHK ለሚቀርብላቸው የአስቸኳይ ጊዜ ሕክምና እና ሕክማዊ ወሳኝነት ያለው ሕክምና የገንዘብ እገዛ የሚያገኙበት አሰራር መዘርጋትም የገንዘባዊ እገዛ ፖሊሲው አላማ ነው።

2. ለሚቀርቡላቸው አገልግሎቶች ሙሉ ክፍያ መፈጸም ለማይችሉ ግለብዎች MHSHK የገንዘብ እርዳታ እንዲያቀርብ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች እና የማመልከቻ አቀራረብ ሂደትንም በገንዘባዊ እገዛ ፖሊሲው ተለይተው ቀርበዋል።

3. ይህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ በ MHSHK ሆስፒታል የሚሰጡ የአስቸኳይ ወይንም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ሕክምናዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ይህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ከሆስፒታሉ ውጪ በሚገኙ የሕክምና አገልግሎቶች አቅራቢዎች እና የሐኪሞች አገልግሎቶች ላይ የጸና አይሆንም። በገንዘብ እገዛ ፖሊሲው ሽፋን ስር የአስቸኳይ ጊዜ እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ሕክምናዎች የሚሰጡ የሆስፒታል ተቋሙ አቅራቢዎች እና ከገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ሽፋን ውጪ አገልግሎቶች የሚሰጡ አቅራቢዎች ዝርዝር ድረገጻችን ላይ ማግኘት ይችላሉ፦ http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program/። ነጻ

የወረቀት ቅጂዎችም በጥያቄዎ መሰረት በሆስፒታሉ የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት መመዝገቢያ ቦታዎች ማግኘት ይችላሉ። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይንም በ (281) 312-4012 ወይም በ 281-312-4000 በመወደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

4. MHSHK የገንዘብ እገዛ ቅናሽ በሚኖርበት ጊዜ ለማስላት የሚጠቀምበት መስፈርት MHSHK ይህንን የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ የ MHSHK አገልግሎት ተጠቃሚ በሆነው ማህበረሰብ ውስጥ በሰፊው ለማስተዋዋቅ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ የገንዘብ እገዛ ተጠቃሚ የመሆን ብቁነት ለመወሰን MHSHK የሚከተለው ሂደት፣ እና የገንዘብ እገዛ ማመልከቻ ሂደት በሚመለከት የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው ማብራሪያ ይዟል። MHSHK ክፍያ በማይፈጸምባቸው አጋጣሚዎች የሚወስዳቸው እርምጃዎች MHSHK በተባለው ሌላ ፖሊሲ ላይ ተገልጸዋል፣ ይህ ፖሊሲ ከ MHSHK ድረገጽ ላይ ማውርድ (ዳውንሎድ ማድረግ) ይቻላል፡- http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program፣ ወይንም ነጻ የወረቀት ቅጂ የአስቸኳይ ህክምና ዲፓርትመንቱ ላይ እና የሆስፒታሉ መመዝገቢያ ቦታዎች ላይ ይገኛል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይንም በ (281) 312-4012 ወይም በ 281-312-4000 በመወደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

5. ለገንዘባዊ እገዛ ብቁ ለመሆን፣ ታካሚዎች የገንዘብ እገዛ ማመልከቻ ሞልተው (በአሳማኝ ግምት ብቁ ናቸው ተብሎ ለማይታመንባቸው ታካሚዎች) ከሁሉም አስፈላጊ ተጨማሪ ሰነዶች ጋር ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል። የገንዘብ እገዛ ማመልከቻዎች የመጀመሪያው እርስዎ የገንዘብ እገዛ ለጠየቁባቸው አገልግሎቶች የሚሆን የመጀመሪያ የክፍያ መግለጫ ከተላለፈበት ቀን አንስቶ ከ 240 ቀናቶች በማይረዝም ጊዜ ውስጥ ዝግጁ ይሆናሉ። ልዩ ሁኔታዎች በአሰራር ክፍል 9 በተገለጸው መሰረት ሊፈቀዱ ይችላሉ። ዛሬ በተግባር ላይ ከሚገኙትም ይሁን ለወደፊቱ ከሚወጡ የፌደራል እና የአካባቢ ሕጎች በላይ ሊሆን አይችልም።

6. ታካሚው የገንዘብ እገዛ ቅናሽ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ የከፈላቸው ትርፍ ክፍያዎች ካሉ፣ ሁሉም ትርፍ ክፍያ የተከፈለባቸው የሕክምና አጋጣሚዎች ታይተው ትርፍ ክፍያው እንዲመለስለት የሚደረግ ይሆናል።

7. MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ብቁነት ለማረጋገጥ በቂ ጥረት ማድረጉን የማረጋገጥ ሙሉ ስልጣን ለ MHSHK የታካሚ ስራ አገልግሎት ጽሕፈት-ቤት የተሰጠ ነው። ይህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ከርህራሄ እና ወካይነት እሴቶቹ ጋር በሚጣጣም መልኩ የ MHSHK ማህበረሰብን ተጠቃሚ ለማድረግ ነው አላማው። የዚህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ መኖር የገንዘብ እገዛን ለሆነ ታካሚ የማቅረብ ግዴታን አያመለክትም ስለዚህ በውል የሚጸኑ መብቶች ወይንም ግዴታዎች አይፈጥርም። ይህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ በቀጣይ ጊዜ በ MHSHK ሊሻሻል እና በዳሬክተሮች ቦርድ ወይንም እሱ በሚሰጣቸው አቅጣጫ ብቻ በሚሰሩ ተወካዮች ሊጸድቅ ይችላል።

8. እዚህ የተጠቀሱት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ከቴክሳስ ግዛት ሕገ-ደንቦች እና ከውስጣዊ ገቢዎች ኮድ ክፍል § 501(r) እና ተዛማጅ አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥመው መሄድ ይኖርባቸዋል።

***ቃላቶች & ፍቺዎቻቸው፦***

1. *ማመልከቻ፦* በታካሚው የሚሞላ የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ ማለት ነው።

2. *የማመልከቻ ጊዜ፦* በማመልከቻ ጊዜው፣ MHSHK የገንዘብ እገዛ ማመልከቻ ተቀብሎ ያስኬዳል። የማመልከቻ ጊዜው ሕክምናው ለግለሰቡ በተሰጠበት ቀን ተጀምሮ ከመጀመሪያው የህክምናው የክፍያ መግለጫ ቀን በኋላ በ 240 ^ኛው^ ቀን የሚጠናቀቅ ይሆናል።

3. *ጠቅላላ የሚከፈል መጠን (AGB)፦* የገንዘብ እገዛ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች ለአስቸኳይ ሕክምና ወይንም ህክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው ሕክምናዎች የሚጠየቁት የክፍያ መጠን መድህን ያላቸው ሰዎች ከሚከፍሉት አጠቃላይ ክፍያ (AGB) የማይበልጥ ይሆናል።

    a. የ MHSHK የ AGB መቶኛ በ "ወደኋላ-ማየት" ዘዴ የሚሰላ ሲሆን፣ የተፈቀደው ከ Medicare ነጻ-የሆነ-የአገልግሎት ክፍያ በ 12-ወራቶች ውስጥ ለሚጠየቁ ጠቅላላ ክፍያዎች ድምር በማካፈል የሚገኝ ነው። ለገንዘባዊ እገዛ ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች የሚደረጉ ቅናሾች ታካሚዎቹ ከ AGB በላይ ክፍያ አለመጠየቃቸውን ለማረጋገጥ ከ AGB መቶኛ ገደብ አንጻር ይገመገማሉ።

    b. AGB መቶኛዎች በኤግዝቢት A ውስጥ - በአጠቃላይ ክፍያ የተጠየቀባቸው የ FAP ስሌት።

    c. የተሻሻለው የ AGB መቶኛ በየአመቱ የሚሰላ ሲሆን የበጀት አመቱ ከተጀመረ በ 120^ኛው^ ቀን ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

4. *አመታዊ ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ፦* አንድ ቤተሰብ ከሁሉም የስራ ገቢዎች እና የጥሬ ገንዘብ እገዛዎች የሚያገኘው ግብር ያልተከፈለበት ገቢ ላይ ለህጻን እገዛ የሚደረግ ክፍያ በመቀነስ ለዩናይትድ ስቴትስ የውስጥ ገቢዎች አገልግሎት ሪፖርት የሚያደረገው ጠቅላላ አመታዊ ገቢ ነው። የቤተሰብ ገቢ፣ በስራ የሚገኝ ገቢ፣ የስራአጥነት ካሳ፣ የሰራተኛ ካሳ፣ የማህበራዊ ማስተናገ፣ የተጨማሪ ዋስትና ገቢ፣ የመንግስት እርዳታ፣ የውትድርና ተሰናባች ክፍያዎች፣ ከሞት ለተረፉ የሚደረግ ድጎማ፣ የጡሮታ ገቢ፣ ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ፣ በፍርድቤት ትእዛዝ ለድሮ ሚስት/ባል የሚከፈል ክፍያ፣ የህጻን እገዛ፣ እና ከሌሎች ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ያጠቃልላል።

5. *የተመረጡ አገልግሎቶች፦* አስቸኳይ ትኩረት የማይሻ የጤና ችግር ለማከም የሚሰጡ አገልግሎቶች። የተመረጡ አገልግሎቶች ለታካሚው ጥቅም የሚሰጡ ሕክምናዎችን የሚያጠቃልሉ ሲሆኑ፣ ነገር ግን አስቸኳይ ያልሆኑ እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው እና ሕክምናዊ ወሳኝነት የሌላቸው አገልግሎቶች፣ ማለትም መልክን ለማስተካከል ብቻ የሚደረጉ እንደ የውበት እና የጥርስ ቀዶ ጥገና ሕክምናዎች እንዲሁም ሌሎች በህክምና መድህን እቅዶች የማይሸፈኑ የተመረጡ ሕክምናዎችን የሚያካትቱ ናቸው። ህክምናዊ ወሳኝነት የሌላቸው የተመረጡ አገልግሎቶች ለገንዘባዊ እገዛ አይቀርቡም ወይንም የገንዘብ እገዛ አይደረግላቸውም።

6. *የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎቶች፦* ቅጽበታዊ የሕክምና ትኩረት ካልተሰጠው በስተቀር የግለሰቡን (ወይንም፣ ከእርጉዝ ሴት አንጻር ደግሞ፣ ሴትየዋ ወይንም ጽንሱ) ጤንነት ከባድ አደጋ ላይ የመጣል፣ ከባድ የሰውነት አካል ጉዳት የማስከተል፣ ወይንም የሆነ የሰውነት ክፍል በከፍተኛ ደረጃ የማዛባት ዕድሉ የሰፋ ነው ተብሎ የታመነበት አደገኛ የሕክምና ሁኔታ ምልክት (ከባድ ህመምን ጨምሮ) ለሚታይበት ታካሚ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

7. *እጅግ ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs)፦* እነዚህ የሕግ ወይንም የፍርድቤት ሂደትን የሚጠይቁ እንዲሁም እንደ እዳን ለሌላ አካል መሸጥ ወይንም ተቃራኒ የክሬዲት መረጃ ለክሬዲት ኤጀንሲዎች ወይንም ቢሮዎች ሪፖርት ማድረግ የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችን ሊያካትቱ የሚችሉ የአሰባሰብ እርምጃዎች ናቸው። MHSHK ECAs ላይ እጁን አያስገባም፣ የአሰባሰብ ኤጋሮቹም ECAs ላይ እጃቸው እንዲያስገቡ አይፈቅድም። የ MHSHK አሰባሰብ ፖሊሲዎችን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ የ MHSHK ላይ ማግኘት ይቻላል፣ ሌሎች የ MHSHK የዚህ ፖሊሲ ነጻ ቅጂዎች

ደግሞ መስመር ላይ ይገኛሉ፡- http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program/ ወይንም ነጻ ቅጂዎችን በጥያቄዎ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና ዲፓርትመንቱ እና የሆስፒታሉ መመዝገቢያ ቦታዎች ላይ አለያም በ (281) 312-4012 ወይንም በ 281-312-4000 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

8. *ቤተሰቡ፦* ታካሚው፣ የታካሚው ባለቤት/የተመሳሳይ ጋብቻ አጋር፣ የታካሚው ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች (ታካሚው ህጻን ከሆነ)፣ እና ማናቸውም በታካሚው ወይንም የታካሚው ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ቤት ላይ የሚኖሩ የታካሚው ወይንም የወላጁ የገቢ ግብር ተመላሽ ላይ ተጠሪ የሆኑ ጥገኞች።

9. *የፌደራል የድህነት ወለል (“FPL”)፦* አንድ ግለሰብ ዝቅተኛው የድህነት ደረጃ ላይ ነው ተብሎ እንዲፈረጅ የሚያስችል የገቢ መጠን። ይህ የገቢ ደረጃ እንደ የቤተሰብ አባላት ብዛቱ ይለያያል። የድህነት ወለሉ በየአመቱ በዩናይትድ ስቴትስ የጤና ዲፓርትመንት እና የሰብአዊ አገልግሎቶች እየተሻሻለ የፌደራል ሬጂስተር (መጽሔት) ላይ ይታተማል። ለዚህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ አላማ ሲባል፣ በታተሙት መመሪያዎች ላይ የተገለጸው የድህነት ወለል ያልተጣራ ገቢን የሚወክል ነው። ለዚህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ አላማ የሚውለው የፌደራል ድህነት ወለል በየአመቱ ይሻሻላል። የአሁኑ ጊዜ የፌደራል ድህነት ወለሎች በገንዘብ እገዛ ፖሊሲው ላይ ማግኘት ይቻላል።

10. *የገንዘብ እገዛ፦* የገንዘብ እገዛ ማለት በገንዘብ እገዛ ፖሊሲው ላይ የተቀመጠው የገንዘብ እና ሌላ የብቁነት መስፈርት የሚያሟሉ ታካሚዎች በ MHSHK ሆስፒታሎች አማካኝነት ለሚሰጡ ህክምናዊ ወሳኝነት ላላቸው እና አስቸኳይ ሕክምና ለሚጠይቁ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች መክፈያ ይሆናቸው ዘንድ ሆስፒታል ውስጥ በ MHSHK የሚሰጥ የገንዘብ እገዛ ነው። እገዛ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች መድህን የሌላቸው ታካሚዎች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ታካሚዎች፣ እንዲሁም በከፊል የመድህን ሽፋን ያላቸው ሆነው ከቀሪ የሕክምና ክፍያዎቻቸው የተወሰነውን ወይንም ሙሉውን መክፈል የማይችሉ ታካሚዎችን ያጠቃልላል።

11. *ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች፦* እነዚህ አገልግሎቶች በዋናነት ለታካሚው ወይንም ለሐኪሙ ምቾት ሲባል ሳይሆን አንድን የሕክምና ወይንም የጤና ችግር ለመመርመር፣ በቀጥታ ለማከም፣ እና ለመንከባከብ የሚሰጡ፣ በአካባቢው የተቀመጡ የጥሩ ሕክምና መመዘኛዎችን የሚያሟሉ እና በ Medicare እና Medicaid ፕሮግራሞች ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ተብለው የሚወሰዱ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶች ናቸው። ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች የውበት ቀዶ ጥገና ወይንም እንደ ማህበራዊ፣ ትምህርታዊ ወይንም የሙያ ስልጠና አገልግሎቶች የመሳሰሉ ሕክምናዊ ያልሆኑ አገልግሎቶችን አያጠቃልሉም።

12. *በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ (“PLS”)፦* የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- (a) የብቁነት መስፈርቶች እና የሚሰጠው እገዛ አጭር መግለጫ፡- (b) የገንዘብ እገዛ ማመልከቻዎች መውሰድ የሚቻልባቸው የድረገጽ እና አካላዊ መገኛዎች ዝርዝር፡- (c) ነጻ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው ቅጂ እንዴት መውሰድ እንደሚቻል የሚያሳዩ መመሪያዎች፡- (d) የማመልከቻ ሂደቱ ላይ እገዛ የሚጠይቁበት አድራሻ የያዘ መረጃ፡- (e) የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው በሌላ ቋንቋ ተተርጉሞ የሚያገኙበት እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች፡- እንደዚሁም (f) የገንዘብ እገዛ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች በአጠቃላይ ለአስቸኳይ ሕክምና ወይንም ህክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው ሕክምናዎች ከሚጠየቁት የክፍያ መጠን የበለጠ ክፍያ እንደማይጠየቁ የሚያረጋግጥ መግለጫ።

13. *በቂ ጥረቶች፦* MHSHK ታካሚው ከሆስፒታል ከመውጣቱ በፊት የገንዘብ እገዛ ፖሊሲውን የሚመለከት በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ ለታካሚው በመስጠት ለታካሚው የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ በሚመለከት ማሳወቂያ ለመስጠት በቂ ጥረት ያደርጋል። በተጨማሪም፣ MHSHK ታካሚዎችን ስለ የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ለማሳወቅ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡-

    a. *ያልተሟሉ ማመልከቻዎች፦* ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቡ ያልተሟላ ማመልከቻ ቢያስረክቡ፣ ምን ተጨማሪ መረጃ ወይንም ሰነድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ MHSHK ይልክላቸዋል።

b. *የተሟሉ ማመልከቻዎች፦* MHSHK ለማግኘት ብቁ መሆኑ ወይንም አለመሆኑ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ በተገቢው ጊዜ ይሰጣል እንዲሁም ይህ ውሳኔ የተወሰነባቸው ምክንያቶችን ለታካሚው (የሚቻል ከሆነ፣ ታካሚው ብቁ የሆነበት እገዛ በመግለጽ ጭምር) በጽሑፍ ያሳውቃል። ይህ ማሳወቂያ፣ የተፈቀደው የገንዘብ እገዛ መቶኛ መጠን (ተቀባይነት ላገኙ ማመልከቻዎች) ወይንም ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገባቸው ምክንያት(ቶች)፣ የሚያስኬድ ከሆነ ደግሞ ከታካሚው እና/ወይንም ከቤተሰቡ የሚጠበቀው ክፍያ የሚያጠቃልል ይሆናል። ታካሚው እና/ወይንም ቤተሰቦቹ ሞልተው ያስረከቡት ማመልከቻ በሚገመገምበት ጊዜ መግለጫዎች ይላክላቸዋል።

c. *የታካሚ መግለጫዎች፦* MHSHK የታካሚው ሂሳብ እና የሚከፈለው መጠን የሚገልጹ ተከታታይ መግለጫዎችን ይልካል። የታካሚው መግለጫዎች ታካሚው የመድህን ሽፋን ካለው ለ MHSHK ማሳወቅ እንዳለበት የሚያሳስብ ጥያቄ፣ የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ እገዛ ለመጠየቅ የሚጠቀሙበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው ሰነዶች የሚገኙበት ድረገጽ የሚያካትቱ ናቸው።

d. *የ* MHSHK *ድረገጽ፦* MHSHK ድረገጾች የገንዘብ እገዛ መኖሩን እና የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ ሂደትን የሚገልጹ ማሳወቂያዎች በስፋት በሚታወቅ ቦታ ላይ ይለጥፋሉ። MHSHK ይህንን የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር በቀላል ቋንቋ ከተዘጋጀ ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና ጋር የ MHSHK ድረገጽ ላይ ይለጥፋል፦ http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program/። MHSHK የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች በጥያቄዎ መሰረት እንዲያገኙ በ አስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና በመመዝገቢያ ቦታዎች ያዘጋጅላቸዋል።

14. *በቂ ያልሆነ መድህን ያለው ታካሚ፦* ሙሉ ወይንም ከፊል የመድህን ሽፋን ያለው ሆነው ሲያበቁ ለአስቸኳይ ህክምና ወይንም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያለው ህክምና የሚያወጡት ወጪ የመድህን ክፍያው ከሚሸፍነው በላይ ሲሆንባቸው ቀሪ ክፍያዉን ከኪሳቸው ለመሸፈን በቂ የገንዘብ አቅም የሌላቸው ታካሚዎች ናቸው።

15. *መድህን የሌለው ታካሚ፦* ሙሉም ይሁን ከፊል የጤና መድህን ፖሊሲ ሽፋን የሌለው እንዲሁም የመንግስት ወይንም የግል የጤና መድህን፣ የጤና አበል፣ ወይንም ሌላ የጤና ሽፋን ፕሮግራም (የግል መድህን፣ Medicare፣ ወይንም Medicaid፣ ወይንም የወንጀል ሰለባዎች እገዛ እና ሌሎችም ጭምር) ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ሆኖ ሲያበቃ፣ የደረሰበት ጉዳት በሰራተኞች ካሳ አሰራር መሰረት ሲታይ ካሳ ሊከፈለው የማይችል፣ ወይንም በእዳ ወይም በሶስተኛ አካል መድህን ምክንያት ሊካስ የማይችል መሆኑን ታካሚው ራሱ ባቀረባቸው መረጃዎች ወይንም በ MHSHK ለሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ ሲባል ከሌሎች ምንጮች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ MHSHK ያረጋገጠበት ታካሚ ነው።

***<u>የግምገማ መስፈርት</u>፦***

1. *ተግባቦት፦* ታካሚዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ማህበረሰቡ የገንዘብ እገዛ ስለመኖሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ MHSHK ወደ ሆስፒታሎቹ የሚመጡ ታካሚዎችን እና ጎብኚዎችን የገንዘብ እገዛ መኖሩን እንዲያውቁ እና ይህንን የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ለሚጠቀመው ማህበረሰብ በሰፊው ለማስተዋወቅ ብዙ እርምጃዎች ይወስዳል። እነዚህ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

a. *የታካሚ ስምምነት፦* የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ለማግኘት በሚመዘገቡበት ጊዜ የሚፈረመው የጤና እንክብካቤ ስምምነት የበጎ አድራጎት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ከሆነ፣ ልክ ወደ ሆስፒታል እንደገቡ ወይንም ዝርዝር የክፍያ ደረሰኞች ወይ መግለጫዎች በሚያቀርቡበት ጊዜ የብቁነት ጥያቄ መቅረብ አለበት የሚል መግለጫም ያጠቃልላል።

b. *የገንዘብ ምክር አገልግሎት፡-* የ MHSHK ታካሚዎች የሆስፒታሉ ክፍያ ድርሻቸውን መክፈል እንደማይችሉ በሚገምቱበት ጊዜ ከሆስፒታል የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ መረጃ እንዲጠይቁ ይበረታታሉ። የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪዎቻችን መድህን ለሌላቸው፣ በቂ መድህን ለሌላቸው፣ ወይንም እኛ ለምናቀርብላቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ክፍያዎች ከመክፈል ጋር በተያያዘ ሌላ የገንዘብ ተግዳሮቶች ላጋጠሙዋቸው ታካሚዎች ለመርዳት የቻሉትን ሁሉ ይጥራሉ። የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪዎች ታካሚዎችን ለተለያዩ በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰሩ ፕሮግራሞች የብቁነት ማጣሪያ ሊያደርጉባቸው፣ የሰራተኛ ካሳ ወይ እዳ ጥያቄ ላይ ትብብር ሊያደርጉ፣ የክፍያ አከፋፈል እቅድ ሊያራዝሙ፣ ወይንም ታካሚዎች የገንዘብ እገዛ እንዲጠይቁ ሊተባበሩዋቸው ይችላሉ።

c. *በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ እና ማመልከቻ፡-* የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው በቀላል ቋንቋ የቀረበ ጥቅል መረጃ የወረቀት ቅጂ እና የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻው የወረቀት ቅጂ ሁሉም ታካሚዎች አገልግሎት በሚያገኙበት ጊዜ ቶሎ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። MHSHK የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች በጥያቄዎ መሰረት እንዲያገኙ በ አስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና በመመዝገቢያ ቦታዎች ያዘጋጅላቸዋል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይንም በ 281-312-4012 ወይም በ 281-312-4000 በመደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

d. *የተተረጎሙ ቅጂዎችም አሉ፡-* MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው፣ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀው ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻው፣ እና የኢንግሊዝኛ ብቃት ውስኑነት ላላቸው ከአምስት በመቶ (5%) የሚያንሱ ወይንም ለ 1,000 የሆስፒታሎቹ ተገልጋይ የማህበረሰቡ አባላት ተርጉሞ ይሰጣል። MHSHK የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎችን የ MHSHK ድረገጽ ላይ እንዲሁም ከአስቸኳይ ሕክምናዲፓርትመንቱ እና ከሆስፒታል መመዝገቢያዎ ቦታዎች ላይ ጠይቀው ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይንም በ 281-312-4012 ወይም በ 281-312-4000 በመወደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

e. *አመልካች ማሳወቂዎ፡-* ሁሉም የገንዘብ እገዛ አመልካች ማሳወቂያዎች በ MHSHK የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና የታካሚዎች መመዝገቢያ ቦታዎችን ጨምሮ ለህዝቡ በግልጽ በሚታዩ ቦታዎች በግልጽ እና በጉልህ፣ እንደሚታዩ ሆነው አመልካች ማሳወቂያው የገንዘብ እገዛ መኖሩን እና ተጨማሪ መረጃ ለመጠየቅ የሚያስችሉ የእያንዳንዱን የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ ስልክ ቁጥር ያሳያሉ።

f. *ድረገጽ፡-* የ MHSHK ድረገጾች የገንዘብ እገዛ መኖሩን የሚገልጽ ማሳወቂያ ከገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻው አሰራር ማብራሪያ ጋር በማድረግ ብዙ ሰው በሚያውቀው ቦታ ይለጥፋሉ። MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲውን ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር፣ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀው ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና የ MHSHK ድረገጽ ላይ ይለጥፋል፡- [http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program/](http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program/)።

g. *የታካሚ ክፍያ መጠየቂያዎች እና መግለጫዎች፡-* የታካሚ መግለጫዎች ታካሚው ማንኛውም አይነት የጤና መድህን ካለው ለ MHSHK የማሳወቅ ሃላፊነት እዳለበት የሚገልጽ ጥያቄ የሚያካትቱ ሲሆን; የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ እገዛ የሚጠይቁበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ እገዛ ሰነዶች የሚገኙበት የድረገጽ አድራሻ ጭምር ያጠቃልላሉ።

h. *ፖስታ ወይም ፋክስ፡-* ታካሚዎች የእነዚህን ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች ለማግኘት ሙሉ ስማቸውን እና MHSHK ቅጂዎቹን እንዲልከላቸው የፖስታ ምላሽ መላኪያ አድራሻቸውን በማካተት ከታች ወዳለው አድራሻ የጽሑፍ ጥያቄያቸውን በፖስታ ወይንም በፋክስ መላክ ይችላሉ።

Memorial Hermann Surgical Hospital Kingwood
Attn: Financial Assistance
300 Kingwood Medical Drive
Suite 100
Kingwood, Texas 77339
ፋክስ፦ 281-358-2461

2. *ብቁነትን መወሰን፦* የገንዘብ እገዛ ውሳኔ የሚተላለፈው የግለሰቡ የገንዘብ ፍላጎት ግምገማ አሰራርን በመከተል ነው። እነዚህ አሰራሮች ከታች ተገልጸዋል፦

   a) ታካሚው ወይንም እርዳታ ሰጪው በማጣራት ሂደቱ የመተባበር እንዲሁም የአሳማኝ ግምት ብቁነት ለመወሰን የሚያስፈልጉ የግል ወይንም ገንዘባዊ መረጃ እና ሰነድ እንዲያቀርቡ የሚጠበቁበት የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ ሂደት፦

   b) MHSHK የአንድን ግለሰብ የ ገንዘብ እገዛ ፖሊሲ-ብቁነት ለመወሰን በቂ ጥረት ካደረገ በኋላ ግለሰቡ ከሆስፒታል ከመውጣቱ በፊት የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲን የሚያብራራ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ የያዘ ማሳወቂያ ለታካሚው ለመስጠት ጭምር በቂ ጥረት ያደርጋል። በተጨማሪም፣ MHSHK ታካሚዎችን ስለ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ለማሳወቅ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፦

      i) *ያልተሟሉ ማመልከቻዎች፦* ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቡ ያልተሟላ ማመልከቻ ቢያስረክቡ፣ MHSHK የመጀመሪያው ማመልከቻ በተቀበለ በአርባ አምስት (45) ቀናቶች ውስጥ ምን ተጨማሪ መረጃ ወይንም ሰነድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ ይልክላቸዋል።
      ii) *የታካሚ መግለጫዎች፦* የታካሚ መግለጫዎች ታካሚው ማንኛውም አይነት የጤና መድህን ካለው ለ MHSHK የማሳወቅ ሃላፊነት እዳለበት የሚገልጽ ጥያቄ የሚያካትቱ ሲሆን፣ የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ እገዛ የሚጠይቁበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ እገዛ ሰነዶች የሚገኙበት የድረገጽ አድራሻ ጭምር ያጠቃልላሉ።
      iii) *የ* MHSHK *ድረገጽ፦* የ MHSHK ድረገጾች የገንዘብ እገዛ መኖሩን የሚገልጽ ማሳወቂያ ከገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻው አሰራር ማብራሪያ ጋር በማድረግ ብዙ ሰው በሚያውቀው ቦታ ይለጥፋሉ። በ MHSHK ድረገፅ፦ http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program/, MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲውን ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር፣ ከቀላል ቋንቋ ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና ይለጥፋል።
      iv) *ሰነዶች ጠይቆ መውሰድ ይቻላል፦* MHSHK ነጻ፣ የ FAP የወረቀት ቅጅዎችና ሽፋን ያላቸው እና በ FAP ሥር ሽፋን የሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር፣ የቀላል ቋንቋ አጭር መግለጫ፣ የፋይናንስ ድጋፍ ማመልከቻ፣ የክፍያ መጠየቅ እና መሰብሰብ ፖሊሲ፣ በድንገተኛ ክፍል እና መመዝገቢያ አካባቢዎች ውስጥ በነጻ ያቀርባል።

   c) በ TransUnion ወይንም Experian የመበደር አቅምዎ ጨምሮ የታካሚው ወይንም የእርዳታ ሰጪው የመክፈል ብቃት የሚሳዩ ይፋ የሆኑ ውጫዊ ዳታዎችን መጠቀም፣

   d) ቀደም ሲል በ MHSHK ለተሰጡ አገልግሎቶች መክፈያ ሊሆኑ የሚችሉ የታካሚው ያልተከፈሉ ሒሳቦችን እንዲሁም የታካሚው ክፍያዎች እና ሊመለሱ የማይችሉ ወይንም የባከኑ ብድሮችን መገምገም፣

   e) በ MHSHK የሚሰጥ የገንዘብ እገዛ ደረጃዎች የ ገቢ፣ የቤተሰበ አባላት ብዛት፣ እና የፌደራል ድህነት ወለል ላይ የተመሰረተ ነው። መድህን ያላቸው እና የሌላቸው ታካሚዎች ሁለቱም የገንዘብ እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፣ እንደዚሁም።

   f) የአንድን ታካሚ የገንዘብ እገዛ ብቁነት ከታች ያለው መስፈርት ላይ የተመሰረተ ሲሆን እንደ ታካሚው የገንዘብ አቅም ሁኔታ፣ እየቀነሰ የሚሄድ የገንዘብ አቅም ሁኔታ፣ እንዲሁም የሶስተኛ አካል የጤና ጥቅማጥቅሞች ከመኖር

ጋር በተያያዘ የተለያየ የብቁነት መመሪያዎች በየአመቱ የፌደራል ድህነት ወለል መመሪያዎች በፌደራል መንግስት ከታተሙ በኋላ ይሻሻላሉ። ከታች ከተጠቀሱት መመሪያዎች የሚልቅ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ለክፍያ እቅድ ከግምት እንዲገቡ የማጣራት ስራ ሊሰራባቸው ይችላል።

3. *የታካሚ ገንዘባዊ እገዛ ብቁነት፦* በፌደራል ድህነት ወለሎች መሰረት፣ የሚከተለው መስፈርት ለገንዘባዊ እገዛ ብቁ ለሆኑ መድህን የሌላቸው እና በቂ መድህን የሌላቸው ታካሚዎች የሚደረግ ቅናሽ ለመወሰን ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል። በቂ መድህን የሌላቸው ታካሚዎች ለበጎ አድራጎት ብቁ ከመሆናቸው በፊት መድህናቸውን ማስከፈል ይጠበቅባቸዋል። ለገንዘባዊ እገዛ ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች የሚደረጉ ቅናሾች ታካሚዎቹ ከ AGB በላይ ክፍያ አለመጠየቃቸውን ለማረጋገጥ ከ AGB መቶኛ ገደብ አንጻር ይገመገማሉ።

   a. **ነጻ ሕክምና፦**

      i. መድህን የሌለው ታካሚ አመታዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢ ያልተጣራ ገቢ ገንዘባዊ ድጋፍ ብቁነት ሰንጠረዥ ላይ እንደተገለጸው፣ ከአሁን የፌደራል የድህነት መመሪያዎች አንጻር በመቶኛ ሲሰላ ሁለት መቶ (200%) ወይንም ያነሰ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣ (ኤግቢት A - በአጠቃላይ ክፍያ የሚጠየቅባቸው መጠኖች ስሌት)፣ ታካሚው (ሌላ ሀላፊነት የሚወስድ አካል) ነጻ ሕክምና (100% ቅናሽ) የማግኘት መብት ስለሚሰጠው ምንም ያልተከፈለ ቀሪ ሒሳብ አይኖሮውም።

      ii. በ Medicare አማካኝነት አንደኛ ደረጃ የጤና ሽፋን የሚያገኙ ሆነው ሲያበቁ በ Medicaid አማካኝነት ደግሞ ለሁለተኛ ሽፋን ብቁ የሆኑ ታካሚዎች የ Medicaid ክፍያ ከተከፈለልዎ እና ከ THMP ወይንም ከ Managed Medicaid ከፋይ የሚጠይቁት ክፍያ ተወስኖልዎ ከተቀበሉ በኋላ ለሚቀረው ያልተከፈለ ሒሳብ መጠን መቶ ፐርሰንት (100%) ቅናሽ ብቻ ይደረግልዎታል።

   b. **ቅናሽ የተደረገበት ሕክምና፦**

      i. ከአሁኑ የፌደራል የድህነት መመሪያዎች አንጻር ሲታይ ከሁለት መቶ ፐርሰንት (200%) የሚልቅ ከአራት መቶ ፐርሰትንት (400%) ግን የማይበልጥ ያልተጣራ አመታዊ የቤተሰብ ገቢ ያላቸው ታካሚዎች/ግለሰቦች መድህን ያላቸው ታካሚዎች ከሚከፍሉት ጠቅላላ የክፍያ መጠን (AGB) የሚስተካከል ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

      ii. በሆስፒታል ወጪያቸው ላይ ያልተከፈለ የሂሳብ መጠን ያላቸው ታካሚዎች፣ የሚከተሉትን መስፈርቶች ሁሉ ከተሟሉ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፦ 1) የሒሳብ መጠኑ ከግለሰቡ አመታዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢ አስር በመቶ (10%) የሚበልጥ ከሆነ፣ 2) ቀሪ ክፍያውን በሙሉ ወይንም በከፊል መክፈል የማይችሉ ከሆነ፣ እንደዚሁም 3) ያልተከፈለው የሒሳብ መጠን ቢያንስ $5,000 ሲሆን። በእነዚህ አጋጣሚዎች ጊዜ፣ ታካሚው ወይንም ተያዡ ከገንዘባዊ እገዛ ፖሊሲው ሂደት ጋር መተባበር እና የብቁነት ውሳኔ ለመወሰን የሚያስፈልጉ የግል መረጃዎች እና ሰነዶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ከጸደቀ፣ ታካሚው ለቀሪው ያልተከፈለ የሂሳብ መጠን ከዓመታዊ አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢው ከአስር ፐርሰንት (10%) ያልበለጠውን ብቻ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፣ ወይም የ AGB ቅናሽ ይተገበራል። ከሁለቱ ያነሰው እና ለታካሚው የፋይናንስ ሁኔታ ጠቃሚ የሆነው ይተገበራል።

4. *የቡቅነት የጊዜ ሰሌዱ፡-*

    a. መድህን ለሌላቸው ታካሚዎች፣ የገንዘብ እገዛ እና የአሳማኝ ግምት ብቁነት ውሳኔ ለሁሉም በታካሚው ሊከፈሉ ክፍት የነበሩ የሒሳብ መጠኖች ወደኋላ ጭምር ተመልሶ እንዲሁም አሁን እየተሰጡ የሚገኙት ሕክምናዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። የታካሚዎች ብቁነት በአሰራር ክፍል 3 ላይ በተቀመጡት ወሳኝ ምክንያቶች መሰረት የሚወሰን ሲሆን ፈጣን ወይንም ያልዘገዩ ክፍያዎች አድርገው በመቆየታቸው ማግኘት የነበረባቸውን ጥቅም አያሳጣቸውም። በተጨማሪም፣ የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ የሞላ ታካሚ ደግሞ ታካሚው ምንም ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ ሳያስፈልገው ለስድስ ወራት ያህል ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ ተጨማሪ የገንዘብ እገዛ ያገኛል። ማናቸውም ባለፉት ስድስት (6) ወራቶች ውስጥ በታካሚው የገንዘብ አቅም ሁኔታ ላይ የተፈጠሩ በገንዘብ እገዛ ብቁነት ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተጨባጭ ለውጦች በሚኖሩበት ጊዜ ታካሚው ለውጡ በተከሰተ በሰላሳ (30) ቀናቶች ውስጥ ለ MHSHK ማሳወቅ ይኖርበታል። ታካሚው በቤተሰብ ገቢያቸው ላይ የተከሰተው ተጨባጭ ለውጥ ሳያሳውቁ ቢቀሩ MHSHK ይሰጣቸው የነበረው ማንኛውም የገንዘብ እገዛ ለውጡ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ እንዲያቋርጥ ሊገደድ ይችላል።

5. *አስቸኳይ ሕክምና ወይንም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች፡-* የገንዘብ እገዛው ሆስፒታል ውስጥ ለሚሰጡ የአስቸኳይ ሕክምናዎች ወይንም ሕክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው አገልግሎቶች ብቻ የሚሰጥ ነው። በዚህ ክፍል የተካተቱት ይዘቶች በ ፌደራል ወይንም ግዛት ሕግ ላይ ተመስርቶ የታካሚው የመክፈል አቅም ምንም ይሁን ምን ከግምት ሳይገባ በሚሰጠው የአስቸኳይ ሕክምና እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች ከማቅረብ አንጻር የ MHSHK ግዴታ ወይንም አሰራሮች ላይ ለውጥ ለማድረግ የታሰቡ አይደሉም።

6. *የማመልከቻ ሂደት*

    a. *እንዴት ማመልከት ይችላሉ፡-* የገነዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ ሞልቶ ከተጨማሪ ማጠናከሪያ ሰነዶች ጋር ማስረከብ የግድ ይላል። ነጻ የማመልከቻው ቅጂዎች ከ MHSHK ድረገጽ ላይ ማውረድ ይቻላል፡- [http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program](http://www.memorialhermannkingwood.com/financial-assistance-program)። ነጻ የወረቀት ቅጂዎቹን የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንቱ ላይ እና የሆስፒታሉ መመዝገብያ ቦታዎች ላይ ማግኘት ይቻላል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይንም በ 281-312-4012 ወይም በ 281-312-4000 በመደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

    b. አመልካቾች የሞሉዋቸው ማመልከቻዎችን እና ተጨማሪ ማጠናከሪያ ሰነዶችን ወደ ሆስፒታሉ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ መላክ ወይንም ከታች ወደ ተጠቀሰው አድራሻ በፖስታ መላክ ይችላሉ። ታካሚዎች ወደ መረጃ ዴስክ ሄደው ከገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ ጋር መነጋገር እንደሚፈልጉ በመግለጽ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪውን ማግኘት ይችላሉ። የማመልከቻው አሞላል በተመለከተ ጥያቄዎች ለማቅረብ፣ ማመልከቻው በመሙላት ሂደት እገዛ ስለመጠየቅ፣ ወይንም ያስረከቡት ማመልከቻ በምን ሁኔታ እንደሚገኝ ለማወቅ፣ በአካል ሆስፒታል ድረስ በመሄድ የሆስፒታሎቹ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪዎችን ማናገር ይችላሉ ወይንም በ 281-312-4012 ወይም በ 281-312-4000 መደወል ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

    c. የተሞሉ ማመልከቻዎችን ወዴት መላክ ይችላሉ፡-

Memorial Hermann Surgical Hospital Kingwood<br>Attn: Financial Assistance<br>300 Kingwood Medical Drive<br>Suite 100<br>Kingwood, Texas 77339

-ወይም-

ፋክስ፡- 281-358-2461

d. ለገንዘብ እገዛ ወይንም የአሳማኝ ግምት ብቁነት ከግምት የመግባት ጥያቄዎች በማመልከቻ ጊዜው ውስጥ በሚከተሉት ግለሰቦች ሊቀርቡ ይችላሉ፡- (i) ታካሚው ወይንም ተያገዡ፣ (ii) የታካሚው ወይንም የተያገዡ ተወካይ፣ (iii) የ MHSHK ተወካይ በ ታካሚው/አመልካቹ ፋንታ፣ ወይንም (iv) ታካሚውን የሚከታተል ሐኪም።

e. በዚህ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ሌላ ቦታ ላይ የተገለጹ ከግምት የመግባት ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው፣ ታካሚው ከገንዘብ እገዛ ማመልከቻ ሂደቱ ጋር የመተባበር ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ ህላፊነት አለበት። ይህ የሶስተኛ አካል የጤና ሽፋን የሚመለከት መረጃ ማቅረብ; ሁሉም በመንግስት ወይንም በሌላ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ፣ Medicare፣ Medicaid፣ ሶስተኛ አካል ሀላፊነት የሚወስድበት ክፍያ፣ የወንጀል ሰለባዎች ገንዘባዊ እርዳታ፣ ወዘተ) አማካኝነት የገንዘብ እገዛ የማግኘት ጥያቄ ለማቅረብ ወይንም የታካሚው ለሌላ የገንዘብ እገዛ ብቁ መሆን ለመወሰን የሚያስፈልጉ ሰነዶች እና ማረጋገጫዎች በጊዜው እና ወድያውኑ ማቅረብን ያጠቃልላል። እነዚህን ማድረግ አለመቻል የታካው ለገንዘብ እገዛ ብቁነት የመታየት እድል ላይ አሉታዊ ጫና ሊያሳድር ይችላል። ታካሚዎቹ MHSHK ጥያቄ ካቀረበበት ጊዜ አንስቶ መረጃው፣ ማረጋገጫዎቹ እና ሰነዶቹን በሰላሳ (30) ቀናቶች ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣ አለያም ደግሞ ይህ ሳያደርጉ የቀሩበት አሳማኝ ምክንያት ለ MHSHK ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ከአሳማኝ ግምት ብቁነት በስተቀር፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ የግድ በታካሚው (ወይንም ተያገዡ/ ተወካዩ) ነው መሞላት እና መፈረም ያለበት።

f. የገንዘብ እገዛ መጠየቂያ ማመልከቻ በሚሞሉበት ጊዜ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪው ሊተባበረዎት ይችላል። ታካሚው ከሞተ እና በእሱ ፋንታ ሀላፊነት ሊወስድ የሚችል አካል ለይቶ ማወቅ ካልተቻለ፣ የ MHSHK ተወካይ ጥያቄውን ሊያመነጭ እና የተገኙት መረጃዎች እና ሰነዶች ተጠቅሞ ማመልከቻውን ሊሞላ ይችላል።

7. *የቤተሰብ ገቢ፡-*

a. ታካሚው የቤተሰብ ገቢ ለመመስረት ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ (ሰነዶቹ የሚገኙ ከሆነ) አንድ ወይንም ከአንድ በላይ ማቅረብ ይችላል። የታካሚው ቤተሰብ አባላቶች ውስጥ ከአንድ በላይ ስራ የተቀጠረ ሰው ካለ፣ እያንዳንዱ ሰው የግድ ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

i. በቅርብ ጊዜ የተሞላ የፌደራል ገቢ ግብር ቅጽ፣
ii. የግርብ ጊዜ W-2 እና 1099 ቅጾች፣
iii. የከርብ ጊዜ የክፍያ ደረሰኝ (ወይንም፣ የሚያስኬድ ከሆነ፣ የስራአጥነት መግለጫ ቅጂ፣ የማህበራዊ ዋስትና ደብዳቤ፣ ወዘተ)፣
iv. የጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተፈጸመበት የአሰሪ የክፍያ መግለጫ፣ ወይንም
v. ማንኛውም የቤተሰቡ ገቢ በተመለከተ ከሶስተኛ አካል የተገኘ ማረጋገጫ።

b. ታካሚው ቢያንስ ከላይ ከተጠቀሱት ሰነዶች ውስጥ አንድ የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል (ታካሚውን ጨምሮ) ገቢ የሚያንጸባርቅ ሰነድ ማቅረብ ከቻለ እና ማረጋገጫው ላይ ፊርማውን ካኖረ፣ ታካሚው ሰነዶቹን ማቅረብ በማይችልበት ሁኔታ ደግሞ ማረጋገጫው ላይ ፊርማው ያኖረ ሰው ይህ ማድረግ ከቻለ፣ ሙሉ ሰነዶች አልቀረቡም ተብሎ የገንዘብ እገዛ ማመልከቻው ያልተሟላ ሊባል አይችልም።

c. አመልካቹ የማመልከቻ ማረጋገጫው ላይ መፈረም አለበት። MHSHK በኋላ ላይ አመልካቹ በተጨባጭ የውሸት መረጃ ማቅረቡን የሚያሳይ ማስረጃ ካገኘ ውሳኔውን ሊሰርዝ ወይንም ሊያሻሽል ይችላል።

*ተጨማሪ ሰነዶች፦* የ MHSHK የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ የንብረት ወይንም ወጪዎች ሰነዶች አይጠይቅም። ይሁን እንጂ አመልካቾች የገንዘብ ችግራቸውን በማሳየት ይህንን ችግራቸው ሳያሳዩ ሊያገኙት ይችሉ ከነበረው የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ ብቁነት እኩል ወይንም የበለጠ የገንዘብ እገዛ ለማግኘት ሊረዱዋቸው ይችላሉ ብለው ያመኑባቸው ንብረቶች፣ ወጪዎች፣ ገቢ፣ ያልተከፈለ እዳ፣ ወይንም ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ተጨማሪ ሰነዶችን ለማቅረብ ሊወስኑ ይችላሉ።

8. *የውሸት ወይንም አሳሳች መረጃ፦* አመልካቾች የሕክምና ወጪዎች የመሸፈን አቅማቸው በሚመለከት ሆን ብለውየውሸት ወይንም አሳሳች መረጃ ማቅረባቸው ከተረጋገጠ፣ MHSHK የአመልካቹን የአሁን ወይንም የቀጣይ ጊዜ ማመልከቻዎች ውድቅ ሊያደርግ ይችላል። ሆን ተብሎ ሳይሆን በስህተት የቀረበ የሀሰት መረጃ በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ፣ MHSHK እውነተኛው መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔውን ይሰጣል። አመልካቹ ሆን ብሎ ባቀረበው የውሸት መረጃ መሰረት የገንዘብ እገዛ ማግኘት የጀመረ ከሆነ ደግሞ፣ MHSHK ታካሚው ከዚህ ቀደም የወሰደውን የገንዘብ እገዛ ይሰርዛል፣ እንዲሁም MHSHK ሕጋዊ መብቶቹን በመጠቀም ታካሚው ቀደም ሲል የወሰዳቸው ክፍያዎችን እንዲመልስ ሊያደርግ ይችላል። የሀሰት መረጃው ሆን ተብሎ ሳይሆን ባለማወቅ የቀረበ ከሆነ ደግሞ፣ MHSHK እውነተኛው መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔውን ያሻሽላል።

***<u>ዳግመ-ማጣቀሻዎች፦</u>***

የታካሚ ዝውውር ፖሊሲ (EMTALA and Texas Transfer Act Compliance)
የገንዘብ ስጋፍ ግልጽ ቋንቋ ማጠቃለያ
የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ
የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲ

***<u>ማሳያዎች፦</u>***

ኤግዚቢት A - በአጠቃላይ ክፍያ የሚጠየቅባቸው መጠኖች ስሌት

ኤግዚቢት B - ፌዴራል የድህነት መምሪያ

*ወደሚቀጥለው ገጽ ዞሯል*

## ኤግዚቢት A - በአጠቃላይ ክፍያ የሚጠየቅባቸው መጠኖች ስሌት

በአጠቃላይ ክፍያ የሚጠየቅበት መጠን ማለት MHSHK ለ Medicare ለአገልግሎት-ነጻ ለድንገተኛ ወይም ለአይቀሬ ሕክምና አገልግሎቶች ለክፍያ መጠየቂያ እና ኮድ አሰጣጥ በሚጠቀምበት ሂደት ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከ Medicare የተፈቀደ አጠቃላይ መጠን ለእነዚህ የይገባኛል ጥያቄዎች በአጠቃላይ ክፍያ ለተጠየቀበት መጠን ይካፈላል ከዚያም የ AGB መቶኛን ለማወቅ ቁጥሩ ከ 1 ይቀነሳል።

**AGB % ለ IP (የውስጥ ታካሚ) = Medicare IP የተፈቀደ ክፍያ / Medicare IP አጠቃላይ ክፍያ**
**AGB % ለ OP (ተመላላሽ ታካሚ) = Medicare OP የተፈቀዱ ክፍያዎች / Medicare OP አጠቃላይ ክፍያዎች**

| ተቋም | የውስጥ ታካሚ | ተመላላሽ ታካሚ |
|---|---|---|
| Memorial Hermann Surgical Hospital – Kingwood | 30% | 14% |

የበጀት ዓመት 2019 (ጁላይ 2018 – ጁን 2019) AGB፣ መጠኖቹ እንደሚከተሉት ናቸው:-

**ጠቅላላ የሚከፈል መጠን (AGB):- 14%**

**ጠቅላላ የሚከፈል መጠን (AGB):- 30%**

*ወደሚቀጥለው ገጽ ዞሯል።*

## ኤግዚቢት B – የፌዴራል የድህነት መምሪያዎች

የአጠቃላይ ወርሃዊ ገቢ የገንዘብ እገዛ ሰንጠረዥ የሚከለሰው በፌዴራል የድህነት መምሪያዎች ላይ ለውጦች በሚደረጉ ጊዜ ነው። ሰንጠረዡ በየዓመቱ ይዘመናል።

ያልተጣራ ወርሀዊ ገቢ የገንዘብ እገዛ ብቁነት ሰንጠረዥ ማለት MHSHK በዚህ FAP ስር ይህንን የገንዘብ እገዛ ብቁነት ለመሰን የሚጠቀምበት የአሁኑ የገቢ ሰንጠረዥ ነው።

አጠቃላይ የቤተሰብ የወር ገቢ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ሰንጠረዥ በፌዴራል የድህነት መመሪያዎች እና በ Harris County Hospital District የብቁነት ሰንጠረዥ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ እንዲሁም በየጊዜው አግባብነት ባላቸው የመንግስት ኤጀንሲዎች የሚከለስ እና የተጠቀሰውም ሰንጠረዥ ለግምገማ ክፍት ነው።

እባክዎ ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| **Memorial Hermann Surgical Hospital Kingwood**<br>የአጠቃላይ ገቢ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ሰንጠረዥ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2019 የፌዴራል ድህነት መምሪያዎች (FPG)<br>በቤተሰብ መጠን መሰረት ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ለመሆን የሚያስፈልግ አጠቃላይ ዓመታዊ ወይም ወርሃዊ ገቢ። | | | | | | |
| | 100% የ FPG | | 200% የ FPG | | 400% FPG | |
| የቤተሰብ መጠን | ዓመታዊ ገቢ | ወርሃዊ ገቢ | ዓመታዊ ገቢ | ወርሃዊ ገቢ | ዓመታዊ ገቢ | ወርሃዊ ገቢ |
| 1 | $12,490 | $1,041 | $24,980 | $2,082 | $49,960 | $4,163 |
| 2 | $16,910 | $1,409 | $33,820 | $2,818 | $67,640 | $5,637 |
| 3 | $21,330 | $1,778 | $42,660 | $3,555 | $85,320 | $7,110 |
| 4 | $25,750 | $2,146 | $51,500 | $4,292 | $103,000 | $8,583 |
| 5 | $30,170 | $2,514 | $60,340 | $5,028 | $120,680 | $10,057 |
| 6 | $34,590 | $2,883 | $69,180 | $5,765 | $138,360 | $11,530 |
| 7 | $39,010 | $3,251 | $78,020 | $6,502 | $156,040 | $13,003 |
| 8 | $43,430 | $3,619 | $86,860 | $7,238 | $173,720 | $14,477 |
| *ከ 8 ሰዎች በላይ ለሆኑ ቤተሰቦች፣ የፌዴራል የድህነት መምሪያን ለመለየት ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ሰው $4,420 ይጨመራል።* | | | | | | |